# ቀስተደመና ሬድዮ

*( ከመኢሶን የስነጽሁፍ ዝግጅት ክፍል የቀረበ ትችት )*

(2.11.01)

## መናጢ ድህነት፣የስድ ገበያ ኢኮኖሚና አብዮታዊ ዴሞክራሲ አንድ ም ሶስትም ናቸው!

ዛሬ የአለም አቀፉን የግሎባላይዜሽን ስርአት እየታከከና በሱ እየተገፋ በሃገራችን በ መተከል ላይ ያለው ሊበራልና የልቅ ገበያ ኢኮኖሚ ስርአት መናጢ ድህነትን እያስፋፋ፤ እልፍ አእላፎችን ከሰውነት መስመር እያወጣ፣ ነባር የሆኑትን የኢኮኖሚና ማህበራዊ ችግ ሮች ሳንወጣ በነሱ ላይ አዳዲስ ችግሮች፣አዳዲስ ቀውሶችን እየፈጠረ ህዝባችንን ከሰውነ ት ደረጃ እያወጣ የሚሄድ፣ ኢትዮጵያችንንም እንደአገር ህልውናዋን የሚፈታተን ስድ አ ካሄድ ነው። የመዋቅር ማስተካከያ ፕሮግራም የተባለው ፈሊጥ በኛ አገር እንኩዋን በመቶ ሽህ የሚቆጠሩ ሰራተኞችን ለአስከፊ መራቆት ዳርጎ በያዝነው ሳምንት እንኩዋን የዚህ ግ ፈኛ ሂደት ሰለባ የሆኑ ሰራተኞች እሮሮዋቸውን እያሰሙ እያየን ነው። ወገኖቻችንን ለዚህ ግፍ የዳረጋቸው ፕሮግራም «እልሰራአም» ተብሎ በራሳቸው በአራማጆቹ ከተተቸ ወዲህ አሁን ደግሞ የተጀመረው «ድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ» የተባለው ፈሊጥ ሆኑዋል።

በአለም ደረጃ እዚህ የአለም የገንዘብ ድርጅትና የአለም ባንክ የነደፉልን ስትራቴጂ ውስጥ ለመሳተፍ «የተፈቀደላቸው» ሰባ ሰባት አገሮች ሲሆኑ እስካሁን ድረስ አርባ ሶስት አገሮች «የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ ሰነድ» በሚባል ስም የታወቀ ማመልከቻ ለአለም አቀ ፍ የፋይናንስ ድርጅቶች አቅርበዋል። ከነዚህ ውስጥ የወያኔም መንግስት አለበት። ይህ አ ዲሱ ፈሊጥ ካለፈው «ከስትረክቸራል አጀስትሜንት ፕሮግራም» ተብየ ነገር ውድቀት የተ ማረው ነገር ቢኖር ይበልጥ የገበያ ነጻነት፣ ይበልጥ ፕሪይቤታይዜሽን፣ ይበልጥ የንግድ የካ ፒታልና የውጭ ምንዛሪ ገደብ የለሽ እንቅስቃሴ፣ ያነሰ መንግስታዊ ተሳትፎ ወዘተ ስለሚል በመደህየት ላይ ያለነውን ህዝቦች ችግር ያባብሰዋል እንጂ አይፈታውም።

መናጢና እየሰፋ የሚሄድ ድህነት እስካለ ድረስ ደግሞ ህዝቦች የግድ በግብታዊነት ም ቢሆን ሊቃውሞ ይነሳሉ። ይታገላሉ። ይህንን ብሶት የወለደው የህዝቦች ተቃውሞና ት ግል አለምአቀፉ ስርአትና አገር በቀል ተባባሪዎቹ እንዴት አርገው ይቋቋሙታል?። ሁለት መንገዶች ብቻ ነው ያሉት። አንደኛው መንገድ አገሮች እንደ አገር ህዝቦች እንደ ሰብአ ዊ ፍጡር ታውቀው፣ ዴሞክራሲ በነገሰበት፣ ሰብአዊ መብቶች በተረጋገጡበት፤ የህግ የበላ ይነት በተከበረበት አካባቢ እራሳቸው የልማት አቅጣጫቸውን፣ እራሳቸው በመሰላቸው የል ማት ፍጥነታቸውንና ቅደም ተከተላቸውን የሚቀይሱበት ስርአት እንዲያቋቁሙ ለቀቅ ማ ድረግ ነው። ሁለተኛ በተለያዩ ስሞችና መጠሪያዎች በሚከሰቱ ያገዛዝ ስልቶች አማካኝነት ያገሮችን ሉአላዊነት ደፍሮና እነዚህን መብቶች ከህዝብ ነጥቆ አፋኝ ስርአት ማንገስና በህ ዝቦች ደም፣ እንባና መከራ፤ በሃገር ሉአላዊነትና ህልውና መቃብር ላይ ልቅና ስድ የሆነ ውን የነጻ ገበያ ተብየ ስርአት መገንባት ነው። በሁለቱ መሃከል ሌላ መንገድ የለም።

ድህነትን የሚፈለፍል የኢኮኖሚ ስርአት ድሆችን የሚያፍን የፖለቲካ ስርአት የግድ ያስፈልገዋል። አለበለዚያ አይሰራም። ባጭሩ በሃገራችን በመተከል ላይ ያለው የስድ ገበያ ኢኮኖሚ ስርአት ለመቀጠል እንዲችል የአብዮታዊ ዴሞክራሲ የፖለቲካ ስርአት ያስፈልገ ዋል። ለዚህ ነው የወያኔ መሪዎች ተሃድሶ ብለው ከጠሩት ትርምስምሳቸው መቋጠሪያ ላይ እዛው በዛው «ካፒታሊስት ስርአት መገንባቱ ላይ እንረባረባለን፤ አብዮታዊ ዴሞክራሲን እ ንገነባለን» ሲሉ በሂደታቸው ምንም ቅራኔ የማናየው።

ሌላውን ሁሉ ትተን የዚህን አብዮታዊ ተብየ ዴሞክራሲ ህገ መንግስት መሰረት እን መልከት።ይህንን ሰነድ ገና ከመውጣቱ ከኢትዮጵያ ህዝብ ተሽቀዳድመው የምእራብ አገሮ ች «ዴሞክራሲያዊ» ብለው አሞካሽተውታል። ነገር ግን ደግሞ ጠለቅ ብለው ያነበቡትና

ትንሽ ዘወርወር ብለው ለማነጻጸር ያሞከሩ የሃገራችን ዴሞክራቶች ከታሪክ አንጻር የ1936 እ.ም. የስታሊን፣ የ1987 እ.ም. የኮሎኔል መንግስቱ ሃይለማርያም ህገ መንግስታት በዛሬይቱ አለም ደግሞ በዚህ በስታሊናዊ የህገ መንግስት ቲዎሪ የጸኡት የቻይና፣ የሰሜን ኮርያ፣ የቢ የትናም ወዘተ ህገ መንግስታት ፎቶ ኮፒና አደገኛ ሰነድ ብለው አጋልጠውታል።

የዚች ጽሁፍ አላማ ይህንን ህገ መንግስት ለመተንተን ስላልሆነ በጣም ባጭሩ ሰነዱ በስታሊናዊ የህገመንግስት ቲዎሪ ላይ የተገነባ መሆኑን ለማሳየት አንድ መሰረታዊ ይዘቱን ብቻ እንጥቀስ። የስታሊናዊ የህገመንግስት ቲዎሪ በስልጣን ክፍፍል ወይም «ሴፓሬሽን ኦፍ ፓዎር» መርህ አያምንም። ከዚህ ይልቅ የመንግስት ስልጣን አይከፋፈልም የሚለውን መር ህ በመከተል የሁሉም ነገር ቁልፍ አድርጎ የሚነሳው «ዩኒቲኦፍ ስቴት ፓዎር» ወይም «የ መንግስት ስልጣን አንድ ወጥነት» የሚለውን መርህ ነው። ለዚህም ዴሞክራሲያዊ ህገ መ ንግስታት በተተከሉበት በማንም አገርና በየትም ቦታ የሌለ በስታሊናዊ ህገ መንግስታት ው ስጥ ግን ቁልፍ የሆነ አንቀጽ አለው። ይህውም ከስታሊን የ1936 እ.ም. ህገ መንግስት እስ ከመጨረሻው የሶብየት ህገመንግስት አንቀጽ 108፣ በኮለኔል መንግስቱ ህገ መንግስት አንቀ ጽ 62 በኢህአዴግ ህገ መንግስት አንቀጽ 50 የሰፈረው «የመንግስት ስልጣን ከፍተኛ አካል » የሚባል አካል መኖሩ ነው። ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው እንዲህ አይነቱ «ከፍተኛ የመን ግስት ስልጣን አካል» የሚባል ጭራቅ ነገር ይህንን ህገ መንግስታችንን «ዴሞክራሲያዊ» ብለው ባሞካሹልን አገሮች በአንድኛቸውም የለም። በአሜሪካን ይህ ከፍተኛ የመንግስት አ ካል ተብየ ነገር ማነው? ፕሬዜዳንቱ? ኮንግረሱ? ከፍተኛው ፍርድ ቤት? ማንኛቸውም አይ ደሉም።

በማንኛቸውም ስታሊናዊ ህገ መንግስታት ይህ «የመንግስት ስልጣን ከፍተኛ አካል» ተብየ ነገር ፓርላሜንቱ ነው። በሶብየት ህብረት «ሱፕሪም ሶብየት»፤ በደርግ ዘመን ብሄራ ዊ ሸንጎ በኢህአዴግ ስር የተወካዮች ምክር ቤት። በቲወሪ መልኩ ከታየ ሁሉም የመንግስ ት ስራ በዚህ ከፍተኛ ተብየ አካል ቁጥጥር ስር ነው። ስራ አስፈጻሚውን ይመርጣል ይባ ልለታል። የፍርድ ዘርፉን ይቆጣጠራል ይባልለታል። የህገ መንግስት ቁጥጥር በሱ ስር ነው ይባልለታል። የስልጣን ክፍፍል በቴወሪ ደረጃ እንኳን የለም። በህዝብ የተመረጠ እስከሆነ ድረስ ይህንን ሁሉ ስልጣን ቀልሎ ቢይዝ ምን አለበት ይባል ይሆናል። ይህ ግን የመንግስ ት ስልጣን አንድ ወጥነት የተባለውን ጉድ ሌላ መሰረታዊ ገጽታ መሳት ነው።

የስልጣን ክፍፍል መርህ መሰረቱ ስልጣንን ያግድሞሽ መከፋፈል ሲሆን የመንግስት ስልጣን አንድ ወጥነት መርህ ደግሞ ስልጣንን «በአሻቅብ ውክልና» ወይም «በርቲካል ዴ ልጌሽን» የማስረከብ አደገኛ ሂደት ነው። በዚህ አሰራር መሰረት ይህ «የመንግስት ስልጣን ከፍተኛ አካል» የተባለው ነገር ራሱ ሌላ ከፍተኛ አለበት። በምርጫ ስም ይህ አካል ስል ጣንን ባለሙሉ ስልጣን ከተባለለት ህዝብ ይረከባል። በምርጫ አሸናፊነት ስም ምርጫውን አሸንፍኩ ባዩ አንድ ፓርቲ ስልጣንን ከዚህ አካል (ከፓርላሜንቱ) ይረከባል። በዴሞክራሲ ያዊ መአከላዊነት ስም የዚህ ፓርቲ ማእከላዊ ኮሚቴ ስልጣንን ከፓርቲው ይረከባል። በድ ርጅታዊ ደንብና የአሰራር ቅልጥፍና ስም ፖሊት ቢሮ የተባለው የጥቂት ግለሰቦች ስብስብ ስልጣንን ከማእከላዊ ኮሚቴው ይረከባል። ይህ ደግሞ ዞሮ ዞሮ መጨረሻው ሁሉንም ስል ጣን ለጥቂቶች ብሎም ላንድ ግለሰብ ስለሚያስረክብ ከፍተኛ የመንግስት ስልጣን አካል የ ሚባለው ነገር ምንም አይነት አካል ሳይሆን አንድ ግለሰብ ብቻ ሊሆን የሚችልበት ሁኔታ ይፈጥራል። ትላንት እነስታሊን፣ ኮለኔል መንግስቱ፣ ዛሬ ደግሞ አቶ መለስ።

አባባላችንን በአጭሩ እናጠቃልለውና ዛሬ በወያኔዎች እየተተከለ ያለው የስድ ገበያ ኢኮኖሚ ለህዝባችን እየተባባሰና እየከፋ ከሚሄድ ድህነት ማጣትና መራቆት ሌላ ምንም አ ይስገኝለትም። ድህነትንና መጣትን አሻፈረኝ ብሎ እንሳለሁ ካለ ደግሞ የአብዮታዊ ዴሞክ ራሲ ሰይፍ ባንገቱ ላይ አለበት። ለዚህ ነው በመናጢ ድህነት፣ በስድ ገበያ ኢኮኖሚና ባብ ዮታዊ ዴሞክራሲ መሃከል መተጋገዝ እንጂ ምንም ልዩነት ስለማይታየን «መናጢ ድህነት፣ ስድ ገበያ ኢኮኖሚና አብዮታዊ ዴሞክራሲ አንድም ሶስትም ናቸው» ለማለት የተገደድነ ው።ይህንን ከተረዳን ሁለት መደምደሚያዎች ላይ እንደርሳለን።

አንደኛው መደምደሚያ የውጭ ሃይሎችን ሁኔታ ይመለከታል። ባእዳን ሃያላን የወያኔን መንግስት «ስትረክቸራል አጀስትሜንትን ተቀበል፣ ድርጅቶችን ፕራይቬታይዝ አድርግ፣ ለኢንቬስትሜንት የሚያመቹ ህግጋት አውጣ፣ የካፒታል ገበያህን የውጭ ምንዛሬህን ከቁጥጥር ነጻ አውጣቸው፣ የውስጥ ገበያህን ለኛ ሸቀጣ ሸቀጥ ያላንዳች ቁጥጥር ክፈት፣ በአጭሩ ለነጻ ገበያ ወይም ለለየለት የገበያ ኢኮኖሚ ሃገሪቱን አመቻች አለበለዚያ ብድርም እርዳታም አይኖርም» እያሉ እጁን ሲጠመዝዙና እስካሁን ከሞላ ጎደል የፈለጉትን ሁሉ ሲያገኙ አይተናቸዋል። ነገር ግን በዚያው ጽናትና ቆራጥነት በፖለቲካውም መስክ «ይህንን ስታሊናዊ ህገ መንግስት ወዲያ ጣል፣ የፖለቲካ እስረኞችን ፍታ፣ የፕሬስ ነጻነትን አክብር፣ በዘፈቀደና በግፍ ዜጎችን በጠራራ ጸሃይ አትረሸን፣ ወዘተ ባጭሩ የግለሰብ መብቶች ሙሉ በሙሉ የሚከበሩበት፣ዴሞክራሲ ሙሉ በሙሉ የሰፈነበት፣ የህግ የበላይነት የሚረጋገጥበት ሊበራል ዴሞክራሲ ስርአት አራምድ አለበለዚያ ብድርም እርዳታም አታገኝም» ብለው ሲያስፈራሩና በዚህም ከወያኔ ተኳርፈው እርዳታና ብድር ሲከለክሉ አላየንም። ነገር ግን በዚህ መልክ ለኛ ለዴሞክራቶች የሞት ሽረት የሆነውን የዴሞክራሲ ጥያቄ እነሱ በያዝ ለቀቅ ሲይዙት መገረም የለብንም። ለምን? ምክንያቱ አጭር ነው። አሁን በመተከል ላይ ላለው ግፈኛ የኢኮኖሚ ስርአት አብዮታዊ ተብየው ዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ስርአት ምንም እንቅፋትነት የለውም። እንዲያውም በፖለቲካው መስክ «በጠንካራ» ተብየ መንግስት አማካኝነት «የተረጋጋ» ተብየ ስርአት ከሌለ በኢኮኖሚው መስክ እየተተከለ በመሄድ ላይ ያለው ስድና ግፈኛ ስርአት ከፍተኛ ተቃውሞ ሊያጋጥመው እንደሚችል ያውቃሉ። ከዚህ ሃቅ ከተነሳን በሃገራችን ዴሞክራሲን ለማስፈን ከፈለግን በማንም በማንም ላይ ሳይሆን በራሳችንና በህዝባችን ትግልና መስዋእትነት ላይ ብቻ መተማመን እንደሚያስፈልግ ግልጽ ይሆንልናል።

ሁለተኛው ድምዳሜ እኛኑ ራሳችንን የኢትዮጵያን ዴሞክራቶች የሚመለከት ጉዳይ ነው። ልቅ በሆነ ነጻ ገበያ፣ በተዝረከረከና የህዝባችንንም ከብሉይ ኪዳን ዘመን ድህነት በሚያባብስና የሃገራችንን ሉአላዊነትና ህልውና በሚፈታተን መልኩ እንጓዝ እስከተባለ ድረስ አፋኙ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ የፖለቲካ አወቃቀር የግድ መሆኑን መረዳት አለብን። ይህ ማለት ደግሞ በእንደዚህ አይነቱ ሊበራልና ጸረ ህዝብ የኢኮኖሚ መሰረት ላይ ሁላችንም የምንመኘው የተሟላና የግለሰብ መብቶች ያለአንዳች መሸራረፍ፣ ዴሞክራሲያዊ መብቶች ያለአንዳች ወለም ዘለም፣ የህግ የበላይነት ያላንዳች ገደብ የሚረጋገጡበት የፖለቲካ ስርአት ለመገንባት አስቸጋሪ እንደሚሆን ከወዲሁ መገንዘብ ይቻላል ማለት ነው።

ይህ ማለት ግን ለእንዲህ አይነቱ ዴሞክራሲ መታገል አያስፈልግም ማለት አይደለም። በፍጹም። ዛሬ ከመቸውም ጊዜ ይበልጥ ይህ አይነቱ የተሟላ ዴሞክራሲ ለህዝባችንም ደህንነት ለሃገራችንም ህልውና እንደ ህይወት እስትንፋስ አስፈላጊ ነገር ነው። ጸረ ህዝቦችና ከሃዲዎች እንጂ ብዙሃንና አገር ወዳዶች ከተሟላ ዴሞክራሲ የሚፈሩት ነገር የላቸውም። ይህ አይነቱ ዴሞክራሲ ሰፍኖ በሃገራችን የተረጋጋ ህብረተሰብ ለመፍጠር ከፈለግን ግን በህዝባችንም ሆነ በአለም አቀፍ ኮሙኒቲ ፊት ከወያኔ ይበልጥ «የነጻ ገበያ» አራማጅ፣ከወያኔ ይበልጥ በመተከል ላይ ላለው አዲስ አለም አቀፋዊ ስርአት አጎብዳጅ ሆነን መቅረብ የትም አያደርሰንም። ከዚህ ይልቅ የሃገራችን የኢኮኖሚ እድገት የኢትዮጵያን ሉአላዊነትና ህልውና፤ እንደዚሁም የብዙሃኑን ደህንነት ከቁጥር ለማስገባቱና ከማህበራዊ ፍትህ ጋር በተጓዳኝነት ለመጓዙ አስተማማኝ የሆነ የኢኮኖሚ ስርአት አማራጭ ማቅረብና ለዚህም እውነት መታገል ይኖርብናል። ለእንዲህ አይነቱ ፍትሃዊ ስርአት እስካልታገልን ድረስና የወያኔዎችን የኢኮኖሚ ፖሊሲ ይበልጥ ነጻ፣ ይበልጥ ክፍት አርገን እንቀጥላለን ካልን ወደድንም ጠላንም በዚህ የኢኮኖሚ ስርአት መሰረትነት በህዝባችን ላይ የምንተክለው የፖለቲካ ስርአት የተሟላ ዴሞክራሲያዊ ስርአት አይሆንም። የፈለግነውን መጠሪያ ብንሰጠው «የአብዮታዊ ዴሞክራሲ» ተብየው ነገር ፎቶ ኮፒ ስርአት እንደሚሆን ከወዲሁ መተንበይና የኢትዮጵያንም ህዝብ ማስጠንቀቅ አስቸጋሪ አይደለም።

የመላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ የስነጽሁፍ ዝግጅት ክፍል